# መዘባረቅና ቅጥረኝነት ደራሳ!

## (ታክሎ መቶ አለቃ ተስፋዬ ሻለቃ)

ከ ፡ ጥላዬ አበበ

ወያኔ ቀውሱ እየተባባሰ ሲመጣ፤ የሚይዝ የሚጨብጠውን ሲያጣ ሁሌም አምርሮ የሚዘምተው ዋና ጠላቶቼ በሚላቸው ላይ መሆኑ የታወቀ ጉዳይ ነው። የራሱን የበሸቀጠ ታሪክ ለማደስ ቅጥረኞቹን አሰማርቶ በርካታ መጽሃፎችን ለገበያ እንዳደረሰው ሁሉ ጠላቴ በሚለው ኢሕአፓ ላይም እነ ውዲ ርስቴና ታክሎንም አስማርቷል። ሻዕቢያም በበኩሉ ተስፋዬ ገብረአብን በል ተሰማራ፤ ቅጠፍ ውሸት ጻፍ ዓውራ ያለው ይመስላል። የወያኔ ዋሾዎች እስረኞችን እየቀጠቀጡ ይጠቅመናል የሚሉትን የቪዲዮ ቅንብር በማሰራጨት ላይ ናቸው። መዘባረቅና ቅጥረኛነት ደርቷል-- ምክንያቱ ምስጢር አይደለም።

ከጥቂት አመታት በፊት አርበኛው  አባታችን ኮለኔል አስናቀ እንግዳና ሌሎችም  የክብር እንግዳ ሁነው የተጠሩበትና  እኒም አንዱ ታዳሚ ሁኜ የተሳተፍኩበት ስብሰባ አትላንታ ከተማ ላይ ተደርጎ ነበር፡፡ ከስብሰባው በኋላ ኮለኔል አስናቀ የተወሰነውን ጠርተው ዛሪም ለትግሉ ጽናት እንዲኖረንና ለሃገራችን ለኢትዮጵያ የሚጠቅም ስራ እንድንሰራ ብዙ ምክር እና ምርቃት ለገሱን፡፡ አርበኛው አባታችን የኢትዮጵያን ችግር በውቅቱ ተረባርበን በአንድ ላይ መፍትሂ ባለመስጠታችን በአባትና በልጅ ብቻ የተወሰነ ሳይሆን የልጅ ልጅንም የሚያካትት የትግል እድሜ ላይ ደረስን ብለው ማዘናቸው ትዝ ይለኛል። አርበኛው አባታችንን ያሳዘነው ሕዝባዊ መንግስት አለመመስረቱ ብቻ ሳይሆን ይህን እልህ አስጨራሽ ትግል የሕዝብን ድምጽ አክብረው ማስከበር ያቃታቸውንም የተቃዋሚ ድርጅት መሪዎችን በእሳቸው እድሜ ማየታቸው እንዲሁም እነዚህ በትግሉ ላይ ጽናት የሌላቸው የፖለቲካ ድርጅቶችም አየሩን በሞሉበት ግዜና ወቅት  ኢ. ሕ አ ፓን ለመቀላቀል የሚመጡ ወጣቶችን ለማሸሽ  በኢሕአፓ ላይ የተዛባ  ታሪክ የሚጽፉ ፖለቲከኞችና ታሪክ ጸሃፊዎች እንደሚመጡ ያውቁ ነበርና ሁሉንም በጥንቃቄ እንድናይ ነው በማዘንም የመከሩን፡፡ በእርግጥም በበኩሌ ዛሬ እያየሁት ያለሁት ያኑኑ ነው፡፡

ለምሳሌም ዛሬ አቶ ታክሎ የሚባል ግለስብ ኢሕአፓን ጥላሸት የሚቀባ ታሪክ ጽፎ፤ ሁሉም ነገር የነበረው እኛ እያለን ነበረ፤ እኛ ከወጣን በኋላ ኢሕአፓ የሚባል ነገር የለም እያለን ነው። ታክሎ የኢሕአፓ ድርጅት አባል የሆነው አቶ መርሻ በሱዳን በኢአግ ጊዜ ሲመለምለው እንጂ

ከዚያ በፊትማ በደርግ ጊዜ የአውራጃ አስተዳዳሪ መሆኑ ይደመጣል። አቶ ታክሎ ከአንዳንድ መጽሐፍ ላይ በጥራዝ ነጠቅነት የቃረመውንና (ከአቶ ክፍሉና ከአሳፋሪው ሻምበል ተስፋዬ ርስቴ) እንዲሁም የፈጠራና የውሸታ ታሪኮችን አካትቶ ለመጻፍ ማን አይዞህ እንዳለውና ምን እንዳነሳሳው እውነቱ ወደፊት እንደሚወጣ መጠበቅም አስፈላጊ አይደለም። ታሪክ ብሎ የጫጫረውን ውጥንቅጥ ማረም ብንነሳ ሌላ መጽሐፍ ይወጣዋል ብንል ማጋነን አይሆንም። አቶ ታክሎም ኢሕአፓነት ያልነካው ስለመሆኑና በደርግ ጊዜም የነበረው ስልጣን ምን እንደነበር ብዙ እየተወራ ስለሆነ ሁኔታውን የሚያውቁ ሰዎች በቅርቡ ዘርዝረው ይጽፉታል የሚል ተስፋ አለኝ። ወደ ተነሳሁበት ነጥብ ልመለስ።

አቶ ታክሎ አንድ ጥያቄ ልጠይቅህ። አቶ ሙሃመድ የጠየቁት በጻፉት መጽሐፍ ውስጥ ለምን የስም ስሕተት ተፈፀመ? የሌሎችም ስም ለምንስ አልተካተተም? የሚል ሆኖ እያለ አንተ ግን ከጥያቄው ወጥተህ  ኢ. ሕ አ ፓ የዛሬ 40 ዓመት ከቀይ ሽብር ታሪክ ጋር አብሮ ያከተመ ድርጅት እንደሆነ፤ ብሎም ኢትዮጵያ ውስጥም ይህ ነው የሚባል እንቅስቃሴ አለመኖሩን እጅግ ዘግይቸም ተረድቸአለሁ ብለሀል። አቶ ታክሎ የኢትዮጵያ ህዝብ ኢ. ሕ አ ፓ ከቀይ ሽብር በኋላ ሙሉ በሙሉ የጠፋ ፓርቲ አድርጎ ነው የሚአስበው ስትልም ደምድምሀል። የኢትዮጵያ ሕዝብ እንደዚያ ብሎ ለማስቡ ያለህ ማስረጃ ምንድን ነው? አደራ መጽሀፍህን እያሻሻጠ ያለውን የወያኔውን በረከት ስሞን እንዳይጠራብኝ! በዚህ 40 ዓመት ውስጥ ኢ. ሕ አ ፓ ከቀይ ሽብር ታሪክ ጋር አብሮ ከጠፋ ጋይም ገ/እግዜአብሔር በ1985 ኢ.ም. ጥሎ የወደቀው አዲስ አበባ ሳይሆን ሜልቦርን ነው ልትለን  ነው? ወይስ አበበ አይነኩሉ የባህርዳር ጨርቃ ጨርቅ ፋብሪካ ሃላፊ በ1986 ዓ. ም. የባህርዳር ጨርቃጨርቅ ፋብሪካ ሰራተኞች ስራ አቁመው በባህርዳር ቢተክርስቲያኖች እግዞታ የተረበሸው ወያኔ ከባህርዳር ጨርቃጨርቅ ፋብሪካ 40 በመጀመርያው ቀን፤ በሁለተኛው ቀን ከ50 በላይ ሰራተኞችን ከሰራው በማገድ እግዞታውን ለማቆም የሞከረው አበበ አነኩሉ በወያኔ አፋኞች የጠፋው፡ ሜልቦርን ከተማ ሳይሆን አዲስ አበባ ነው። በ1991 ኣ. ም. በቀለ ሻረው አሚሪካ ሳይሆን፡ ባህርዳር ነው የጠፋው። መ/አ ሙሉጌታ ዓለሙ 1993 ዓ. ም. ለንደን ስይሆን ባሕርዳር ነው ደብዛው የጠፋው።  የኢትዮጵያ ሕዝብ ማን እንደሚታገልለት፣ እንድሚሞትለት አያውቅም ነው የምትለን? ያሳዝናል! ምነው እኛ ወጣቶች ለብልጭልጭ ኮብራ መኪና፣ ለግራውንድ ፓላስ ዋና ቤቶች፣ ለዘመኑ ቆነጃጅት ሴቶችና ለወያኔ እጃችን ሳንሰጥ አንድ እግራችሁ ወደ ጉድጓድ የገባ ሽማግሌዎች በምናምን በጥቅማ ጥቅም አይናችሁን ከእውነቱ ለመጋረድ ትሞክራላችሁ። ያሳዝናል! ህሊና ላለው ሰው።

ታክሎ ተሾመ ለአሊታዊ ትችትም ቢሆን መቅረቡ ክብሩ መሆኑን አላጣሁትም። ለዚህም ነው ታሪክ ብሎ የጫረውን ውዳቂ መጽሃፍ ያልተቸሁት። የፈለገውን ዕውቅና በበኩሌ ያልሰጠሁት። ይህ አንቱ ሲሉት ግብዝነቱ ጨምሮ አንተ ባይ ሰው ታሪክ ብሎ የጻፈው በርታ ያሉት ክፍሎች በኢሕአፓ ላይ ዝመት የሚል የዘመቻ ዕዝ ሰጥተውት መሆኑ አያከራክርም። የደርግን ወንጀል ሆነ የወያኔን ሁሉ በኢሕአፓ አመራር ላይ ሊጭን የሚሞክረው ይህ መሐይም ሌላ መጽሀፍ እያዘጋጀሁ ነው ሲል እያሳቀን ነው። ዓላማው የፈረደበትን የኢሕአፓ አመራር ማውገዝና ማጥላላት ነውና ይህ ተግባር የማን መሆኑን እናውቃለን--የወያኔ ነው ። አቶ ታክሎ ኢሕአፓ አልነበረም--ስለዚህም ስለ ኢሕአፓ የመጻፍም ችሎታም ዕውቀትም የለውም። የጻፈውም ያስቃል - ከገጽ አንድ ጀምሮ። አባል ነኝ ሊል ሲጀምር ደግሞ ለአጭር ጊዜም ቢሆን አንጃ ነበር በተለይ በሱዳን። ለአጭር ጊዜ--ወደ አዲስ አበባ መማላለስ ከመጀመሩ በፊት። ዋና ትኩረቱና ተልዕኮው ግን ዋናውን ኢሕአፓ ማውገዝ፤ ማጥላላትና ከሕዝብ መነጠል ነው። ኢ. ሕ አ ፓ ከቀይ ሽብር በኋላ ድብዛው ጠፋ ብሎ መለፈፍ ምን ይባላል? እስከ፣ ደልጊ አዳኝ ሀገር ጫቆ፣ ቋራ፣ መተከል ወዘተን ለአመታት የተቆጣጠረው የታክሎ አጎት ይሆን? ያን ሁሉ አመት መስዋዕት የተከፈለበትን የፖለቲካ የትጥቅ ትግል ሽምጥጥ አድርጎ መካድስ ታሪክን መተረክ ነው ወይስ ቅጥረኛነትንና ጥላቻን ማራገብ? ለፀረ-ኢትዮጵያው ወያኔ ታማኝነትን ማሰረገጥ። ታክሎ ውዳቂ የብዕር ኩሊ የሚባሉት ዓይነት ነው። በአጭሩ አያ ታክሎ ወደደም ጠላም፤ ተከፈለውም እርጥባን ተሰጠው ሚናው የወያኔ ነው። እረፍ ብሎ የሚመክረው ወይም የሚገስጸው ያጣ የሽማግሌ ቀላል!!

ሌላ በኢትዮጵያ ጠላቶች አይዞህ አይዞህ ተብሎ ለዘመቻ የተሰማራው ተስፋዬ ገብረ አብ የሚባለው ኤርትራዊ ነው። በበኩሌ ግለሰቡን በግልም ሳይሆን በስራው የማውቀው በአዲስ አበባ ነው። በመጀመሪያ የወያኔው እፎይታ መጽሔት አዘጋጅ ሆኖ። የተራራውን ያንቀጠቀጠ ትውልድ ቅጾች አቀነባባሪና አዘጋጅ ሆኖ። ያን መርዘኛ ጸረ ሕዝብ የቡርቃ ዝምታ ጽፎ የወያኔን ጸረ ሕዝብ አጀንዳ ሲያራምድ። ለዚህ ሰውዬ ምሱን ብዙ ተቺዎች ለግሰውታል ። ካልበቃው በሚል ተጨማሪ እነሆ። በበኩሌ ተስፋዬ ገብረ አብ ማለት የወያኔ ቃል አቀባይ ወሬ አናፋሽ ነው ያልኩት ከዓመታት በፊት ነው። እዚያው ከነክንፈና በረከት ጋር ተቃቅፎ ሲስራ ማለት ነው። የዚያን ጊዜ ዋና ተልዕኮው ኢሕአፓን፤ መኢህድንና የአማራውን ህዝብ ማጥላላትና ማጥቃት ነበር ። የተራራ ያንቀጠቀጥየው ትውልድ አምስት ቅጾች ልብ ውለድ በዜና መሰል ሀስቶች (ኢሕአፓ በሱዳን የከፋኝን መሪ ሊገድል ሞከረ!) አጅቦ ሲያቀርብ ይህን መሰረታዊ አፍራሽና ሕዝብን ከፋፋይ ዓላማ ከግብ ለማድረስ ደግሞ እስከዛሬም ትክክል ነው የሚለውን የቡርቃ ዝምታን በሕዝብ ላይ ጣለበት። ይህ መጽሃፍ ተብዬ የጥላቻ ጽሑፍ ዛሬ ከ 77 ብር በላይ በአዲስ

አበባ በወያኔ እየተሸጠ ነው። ተስፋዬ ከወያኔ ተጣላሁ ብሎ፤ ተሰደድኩ ብሎ ሲወጣና የስደተኛው ማስታወሻ ብሎ መጽሐፍ ሲያሳትም በአጻጻፍ ደረጃ ጎብዝ ነውና (ክታክሎ ባውዳድረው የሜልቡርኑን አዛውንት ማጥቃት ይሆንብኛል) ቁም ነገሩን ስተው አጅሓ ያሉት ብዙዎች ናቸው። ተስፋዬ በተለይ በስነጽሁፉ መስክ ራሱን አዋቂና ጥልቅ አንባቢ አስመስሎ ለማቅረብ ቢሞክርም ጠበቅና ጠለቅ አድርጎ ለሚመረምረው ግን ጥራዝ ነጠቅ መሆኑን በቀላሉ የሚረዳው ይሆናል። ያላነበቡትን መጽሀፍ ያነበቡ አስመስሎ ጥቅስን መደርደር ቀላል ነው--ዕድሜ ለጥቅስ መፃሕፍት! ተስፋዬ በመጀመሪያው መጽሐፉና ለድረ ገጾች በሚልካቸው ጽሁፎች አማካይነት የወያኔና የራሱ ጠላቶችን ሊጎዳ ቢሞክርም ( ስዬ አብርሃ፤ ነጋሶ ጊዳዳ፤ አብርሃም በላይ ወዘተ) ስለ ኢሕ አፓ ያለፈው ይብቃል ብሎ ነው መስል ምንም አልተናገረም  ነበር። ተስፋዬ በመሰረቱ የሻዕቢያ መሳሪያ መሆኑን በመጀመሪያ ለመሸፋፍን ሞክሮ ነበር--ግን አልዘለቀም። ሁለተኛውን መጽሀፍ ለመጻፍና ለመጨረስ አስመራ ገብቶ ከርሟል። መረጃውንም አቅጣጫውንም ያስያዙት ሻዕቢያዎች ከመሆናቸው ሌላ፤ ሁለተኛው መጽሀፉ በአሜሪካ፤ አውሮጳና አፍሪካ በቀጥታ የተሸጠው በሻዕቢያ መደብሮችና ሬስቶራንቶች ነው። ይህ ራሱ በቂ ጥቆማን ሰጥቷል። ተስፋዬ ይህን ማንነቱን ለመሸፈን ግንቦት 7 አባል ሆኛለሁ ግን ምስጢር ነው እያለ ቢያደናግርም ዋናው አለቃው ግን አስመራ መገኘቱ ምስጢር አይደለም።  በአጭሩ ተስፋዬ ገብረአብ ጸረ ኢትዮጵያ ሻዕቢያ ነው ።

በበኩሌ ኢሕአፓም ሆነ ሌሎች ለምን ለታክሎ ዋሾ፤ ተስፋዬ ሻዕቢያ፤ ለነ ሀፍረተ ቢስ ቀባጣሪዎች መቶ አለቃ--ሻምበልና ሻለቃ ተገቢውን ምላሽ እንደማይሰጡ አይረዳኝም። ለዝምታ ወርቅ ነውም ልክ ያለው ይመስለኛል። ተስፋዬ በሻዕቢያ ተበረታቶ ወይም በርታ ተብሎ በ ኢሕአፓ ላይ አፀያፊ ዘመቻውን ከፍቷል። የወያኔ ፀር የሆኑ ግለሰቦች ላይ አተኩሮ የቡርቃ ጩኸቱንም ያስተጋባል። የሞተ  ሰው እየጠቀሱ እገሌ ነገረኝ ማለት መቼም አመቺ ዘዴ ነው። አላልኩትም ባይ አስተባባይ የለምና፤ ሊኖር አይችልምና። ተስፋዬ ከሚቹ የወያኔ የጸጥታ ሀላፊና አፋኝ ጋር ቅርበት እንደነበረው ራሱ አምኗል። በታሰሩ ኦነጎች ላይም ስለላ ማካሄዱን ራሱ ጽፏል። በአሁኑ ዙር ደግሞ በአዲስ አበባ ወያኔ ጋር ተቷኩሶ ራሱን የሰዋውን የኢሕአፓ መሪ ገብረ እግዚአብሔር (ጋይም)ን በማንሳት ኢሕአፓ ለወያኔ ኣሳልፎ ሰጠው ብሎ ክንፈ ነገረኝ ሲልም ጽፏል። የጋይም ልጅ ከወያኔ ጋር ሲታኮስ ሞት ያለውም የጋይም ልጅ መኖሩን ለማናውቀው አይ ውሸት እንድንል ገፋፍቶናል ። የተስፋዬ ዋና መልክት ኢሕ አፓን መወንጀል ነው። ሀቁ ግን ጋይምን በአዲስ አበባ አይቶ ለወያኔ የነገረውና ይህንኑ የክህደት ስራ በባሕር ዳር ሊቀጥል የሞከረውን ግለሰብ ኢ ሕ አ ፓ ተገቢውን እርምጃ ወስዶብታል። ድርጅቱ መሪውን

አጋልጦ አስገደለ የሚለው የተስፋዬ ጩኸት በመሰረቱ የሻዕቢያን የቀድሞ የአስመራ ልምድ ወደ ኢ. ሕ አ ፓ ለማስተላለፍ የተደረገ ሙከራ ይመስላል። ይህ ሁሉ ውሸት ለምን? ለምንስ አሁን?

ምክንያቱ ምስጢር አይደለም። ባዕዳንና ሻዕቢያ የኢትዮጵያን ሁኔታ በራሳቸው ለመወሰን እየጣሩ ናቸው። ሻዕቢያ ኦነግንና ግንቦት 7 ን ወዘተ አቀናጅቶ መለስን በቡችሎቹ ሊተካ ይፈልጋል። ይህ ዕቅዱ አልሳካ ሲለው በኤኤፍዲ ውቅት ለውድቀቱ ተጠያቂ አድርጎ ኢ.ሕአፓን እንደከሰሰው ሁሉ ዛሬ ደግሞ ሻዕቢያ ላቀደው መክሸፍ የፈረደበትን ኢ.ሕአፓን ማውገዙን መርጠዋል። አቶ ተስፋዬ ለዚህ ተልዕኮ ዘማች ተብሏልና የሀሰት ዜናዎችንና ክሶችን ማሰራጨቱ የሚጠበቅ ነው። ኢ. ሕ አ ፓ አባላቱንና መሪዎቹን ለጠላት አሳልፎ መስጠት ልማዱ አይደለም። የእሮይታው ተስፋዬ በከንቱ ባይጮህ መልካም ነበር። ይህ የሻዕቢያ መሳሪያ ኢ. ሕ አ ፓን ፣ ተቃዋሚዎችን፣ ስዬ አብርሀን ፣ ነጋሶ ጊዳዳን ፡ አብርሀም በላይን ፣ ውዘተ ነጋ ጠባ የሚዘልፈው የወያኔና ሻዕቢያን ጸረ ኢትዮጵያ ተልዕኮ ለማሳከት ነው።